## ሰ/ ትንበቶች ከሙሴ ሕግና ከእስራኤል ታሪክ ጋር ያላቸውን ዝምድና መረዳት እንዲሁም መቼ እንደተፈ ጸሙ ማጥናት

የብሉይ ኪዳን ሆነ የአዲስ ኪዳን ትንቢቶች ስንተረጉም ከሙሴ ሕግ፣ከእሥራኤል ታሪክና ከቤተክርስቲያን ጋር ተያያዥነት ስላላቸው እነዚህን ነገሮች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለብን:: እንዲሁም ትንቢቶቹ መፈጸም አለመፈጸማቸውን ማረጋገጥ ጠቃሚ ይሆናል::የትንቢቶችን ፍጻሜ ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ ትንቢቱን በተሳሳተ መንገድ ከተረጎሙትና ስሕተት ከፈጸሙት ሰዎች እየጠቀስኩ ትንቢቶቹ ለማን እንደተጻፉና መቼ እንደተፈጸሙ ለመዳሰስ እሞክራለሁ:: ዶ/ር ሐሰን « ክርስቲያን ሙስሊም ውይይት» በተሰኘው መጽሐፋቸው ከገጽ 64-66 ስለ ኢየሱስ መምጣት በዘዳ.18:18 የተጻፈው ትንቢት ስለ ነብዩ መሐመድ ነው በማለት መጽሐፍ ቅዱስን በግድ ለማናገር ሞክረዋል::ቃሉም እንዲህ ይነጠበባል «እግዚአብሔርም አለኝ:- የተናገሩት መልካም ነው:: ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነብይ አስነሳላቸዋለሁ::» መጽሐፍ ቅዱስ በሐዋ.3:17-26 እናሐዋ.7:33-53 ይህ ሙሴን የሚመስልና ይመጣል ተብሎ ትንቢት የተነገረለት ነብይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ትንቢቱም እንደተፈጸመ በግልጽ ተጽፎ ይገኛል:: ቀደም ብዬ በጠቀስኳቸው ክፍሎች በዘዳ.18:18 ላይ የተጻፈው ቃል በቀጥታ ቃል በቃል ተጠቅሶ እናገኛለን:: ትንቢት ከተፈጸመ በኋላ እንደገና መፈጸም አለበት ብሎ ማሰብ የዋህነት ይመስለኛል::

ዶክተር ሐሰን ትንቢቱ ለነብዩ መሐመድ የተጻፈ ለማስመሰልም በሙሴ ፣በነብዩ መሐመድና በክርስቶስ መካከል ተመሳሳይነትና ልዩነቶችን በቻርት የተደገፈ ዘገባ አቅርበዋል:: በመጀመሪያ ደረጃ ትንቢት በማመሳሰል አይተረጎምም:: አንድ የረሱትም ጉዳይ አለ፤ እርሱም በሙሴና በነብዩ መሐመድ መካከል

ያሉትን ልዩነቶች እናመሳስል ቢባል እንኳን በነብዩ መሐመድና በሙሴ መካከል ትላልቅ ልዩነቶች አሉ:: 1ኛ/ ሙሴ እሥራኤላዊ ሲሆን መሐመድ አረብ ናቸው 2ኛ/ ሙሴ ብዙ ተአምራትን አድርጓል ነብዩ መሐመድ ግን በጣም አነስተኛ የሚባል ተአምራት እንኳን አላደረጉም:: 3ኛ/ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋግሮአል፣ ነብዩ መሐመድ ግን አልተነጋገሩም:: 4ኛ/ሙሴ የኤርትራን ባሕር ከፍሎ በተአምር በመሻገር ሕዝቡን በምድረ በዳ 40ዓመት በተአምራት መርተዋል:: ነብዩ መሐመድ ግን እንዲህ ዓይነት ተግባር ፈጽመው አያውቁም:: 5ኛ/ሙሴ የጦር መሪ ሆኖ ሌሎችን ሰዎች በመግደል እምነቱን አላስፋፋም ነገር ግን ነብዩ መሐመድ በመዲና ቆይታቸው ቢያንስ ሦስት ዋና ዋና ጦርነቶችን /የበድር፣የዱሑድ፣ እና የእሁድ /ጦርነት አድርገዋል:: 6ኛ/ ሙሴ በሕፃንነቱ በተአ ምራዊ ሁኔታ ከሞት አምልጧል፣በንጉሥም ቤተመንግሥት አድጓል፣ ነገር ግን ነብዩ መሐመድ በሕፃንነታቸው የመግደል ሙከራ አልተደረገባቸውም፣ ያደጉትም ስድስት ዓመት እስኪሆ ናቸው ከእናታቸው ጋር፣ ከዚያም ሁለት ዓመት ከአያታቸው በኋላም ከአጎታቸው ጋር ነው:: መዘርዘር ካስፈለገ ብዙ እጅግ ብዙ ልዩነቶች መናገር ይቻላል::

ሌላው በዘዳ.18:18 ያለው ቃል ለተሳሳተ ጽሑፋቸው ድጋፍ ሲፈልጉ የሰሩት ስህተት አለ እርሱም «ከወንድሞቻችሁ መካከል» ማለት አረቦች ወይንም እስማኤላዊያን ናቸው ብለዋል:: እስማኤል ወይንም እስማኤላውያን የእሥራኤላውያን ወንድሞች ተብለው አልተጠሩም ወደፊትም አይጠሩም:: በዘፍ.21:12 በሳራና በአጋር መካከል ጥል በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ለአብርሐም ሲናገር አጋርና ልጅዋ እስማኤልን ከቤት እንዲያባርራቸው ካዘዘው በኋላ የአብርሃም ዘር ደግሞ በይስሐቅ እንደሚጠራ ተናግሮታል:: በዚህም መሠረት አብርሃም እስማኤልና አጋር ከቤት እንዳባረራቸው ግልጽ ነው:: ትንሽ ቆይቶም በዘፍ.22:2 እግዚአብሔር አብርሃምን ሲፈትነው አንድ ልጅህን ይስሐቅን ሰዋልኝ በማለት እስማኤል የይስሐቅ ሕጋዊ ወንድም እንዳልሆነ አሳይቷል:: እንዲሁም ወንድሞች የተባሉት አሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገዶች እንደሆኑ በዘዳ.18:1-2 እንዲህ ተጽፎአል፤ «ለሌዋውያን

ካህናት ለሌዊም ነገድ ሁሉ ከእሥራኤል ጋር ድርሻና ርስት አይሆንላቸውም በእሳት ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን መስዋዕቱንና ርስቱን ይበላሉ። በወንድ ሞቻቸውም መካከል ርስት አይሆንላቸውም።» ዶ/ር ሐሰን ወንድሞች የሚለውን ትርጉም ለማወቅ አንድ ምዕራፍ እንኳን ቢያነቡ ትክክለኛውን መልዕክት ያገኙ ነበር። በመሳ.20:13 በተመሳሳይ ሁኔታ ወንድሞች የተባሉት የእሥራኤል ነገዶች እንደሆኑ እንዲህ ይላል «የብንያምም ልጆች ግን የወንድሞቻቸውን የእሥራኤል ልጆች ቃል ሊሰሙ አልወደዱም።» ነብዩ መሐመድ ግን እሥራኤላዊ ሳይሆኑ አረብ ናቸውና ትንቢቱ ለእርሳቸው አለመሆኑ መታወቅ ግልፅ ነው።

በተጨማሪ ዶ/ር ሐሰን በመጽሐፋቸው ከገጽ 70-73 በበዓለ ሃምሳ ቀን የተፈጸመውና በዮሐ.14:16 ስለመንፈስ ቅዱስ መምጣት ጌታ ኢየሱስ የሰጠውን ተስፋ ስለ ነብዩ መሐመድ ነው ብለው ጽፈዋል። ዶክተሩ ሐሳባቸውን ለመደገፍ በፍጹም የማይገናኙና ሊገናኙም የማይችሉትን ነገሮች ለማገናኘት ሞክረዋል። ስለመንፈስ ቅዱስ /አጽናኙ/ መምጣት በዮሐ.14:16 ብቻ ሳይሆን በዮሐ.14:26፣ 15:26፣16:7 እና ሐዋ.1:8 ትንቢት ተነግሮአል።አፅናኝ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ወይንም መሐመድ እንደሆነ ለመረዳት በዮሐ.14:16 -17 ያለውን የእግዚአብሔር ቃል ማጥናት ተገቢ ነው። ከክፍሉ አጽናኝ የተባለው ነብዩ መሐመድ ሳይሆኑ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ስድስት ዋና ዋና ነጥቦች አሉ። 1ኛ/ ለዘለዓለም ከእነርሱ ጋር እንደሚኖር ይናገራል። መሐመድ ለዘለዓለም ከምዕመኖቻቸው ጋር እንዳልኖሩ ማንኛውም ሙስሊም የሚያውቀው ጉዳይ ነው። 2ኛ/ «ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል» በማለት እናንተ የተባሉት ሐዋሪያቶቹ ናቸው። በሐዋ.2:1-4 ስንመለከት አጽናኙ ኢየሱስ ካረገ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነው የመጣው ።ነገር ግን መሐመድ የመጡት ከ500 ዓመት በኋላ ነው፤ ከሐዋርያቶችም አንድ እንኳ አልነበረም። 3ኛ/ «እርሱም አይቻልም፤ በክርስቶስ ያላመኑት ስለማንነቱ በደንብ ሊያወቁት አይችሉም።ነው ነገር ግን መሐመድ መንፈስ ስላልሆኑ በዘመናቸው ሰዎች አይቷቸዋል ማንነታቸውም ለሁሉ የተገለጠ ነው። 4ኛ/, ዓለም «ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ» ነው። ነገር ግን ቃሉ እንደሚለው መንፈስ ቅዱስን

የሚቀበሉት በክርስቶስ አምነው የዳኑ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ 5ኛ/ «ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን ታውቁታላችሁ፡፡» በዚህ ዓረፍተ ነገር ሦስት ነገሮች እናያለን፡፡ አጽናኙ በሐዋርያት ዘንድ ይኖራል፡በውስጣቸው ይሆናል፡እናም እነርሱ ያውቁታል፡፡ነብዩ መሐመድ ግን አንዱንም እንኳን አያሟሉም፡፡6ኛ/ አጽናኝ የሚለው ቃል በግሪኩ ጰራቅሊቶስ (paracletos) እንጂ እነአህመድ ዲዳት እንደሚሉት ፔሪክሉቶስ ( periklutos) አይደለም፡፡ [16] አህመድ ዲዳት ፔሪክሉቶስ ማለት የተከበረ ማለት ስለሆነ በአረብኛው መሐመድ ማለት የተከበረ ማለት ነው፣ስለዚህ ስለ መሐመድ መምጣት የተነገረ ትንቢት ነው በማለት ጽፈዋል፡፡ ፔሪክሉቶስ የሚለው ቃል በየትኛውም የግሪክ መጻሕፍት ውስጥ የለም፡፡ ሚስተር አህመድ ዲዳት ሰዎችን መሰረተ ቢስ በሆነ ጥናት ከማደናገር የተጨበጠ መረጃ ቢያቀርቡ መልካም ነበር፡፡ ፔሪክሉቶስ የሚል ቃል በግሪኩ መጽሐፍ አለ የሚሉት ቢያቀርቡ ለንግግራቸው ተአማኒነት ስለሚኖረው መረጃቸውን እንዲያቀርቡ ላበረታታቸው እወዳለሁ፤ አለዚያ ግን ሰዎችን ከማሳሳት ቢመለሱ መልካም ነው፡፡ይመጣል የተባለው አጽናኝ ኢየሱስ እንዳረገ በሐዋሪያት ዘመን እንደሚመጣ በሐዋ.1:8 እንዲህ ተጽፎአል፡፡« ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ፡፡ «ይህም የተስፋ ቃል ብዙም ሳይቆይ በበአለ ሃምሳ ቀን ሐዋርያት ተሰብስበው ባሉበት እንደመጣ በሐዋ.2:1-4 ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ከዚያ ሰዓት ጀምሮ ሐዋርያት በድፍረት የክርስቶስን ወንጌል መስበክ ጀምረዋል፡፡ የትንቢቱም ፍጻሜ በግልጽ ተጽፎአል፡፡ ትንቢቶች መፈጸም አለመፈጸማቸውን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ተግባር ስለሆነ ይህንንም ለማወቅ ጥናቶችን ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በጣም የሚያስገርመው ዶ/ር ሐሰን በመጽሐፋቸው ከገጽ 63-64 የጻፉት ሐሳብ ነው፡፡ በኢሳ.21:7 «በአህዮች የሚቀመጡትንና በግመሎች የሚቀመጡት » የሚለው ኢየሱስ እና መሐመድ ናቸው ብለዋል፡፡ ኢየሱስ በአህያ ተቀምጦ ወደ

ኢየሩሳሌም ገብቷል፤ነብዩ መሐመድም ወደ ሶሪያ በግመል ለንግድ ይመላለስ ስለነበር ለእነዚህ ሁለት ነብያት እንደተፃፈ አድርገው ጽፈዋል::በመሠረቱ ትንቢቱ የተነገረው ለኢየሱስም ለነብዩ መሐመድም አይደለም፤ ትንቢቱ የተፃፈው ስለባቢሎን ውድቀት በዚያው ዘመን እንደተፈጸመ መጽሐፍ ቅዱሳችን በኢሳ.21:1-10 ባለው ክፍል ያስተምራል:: ስለ ፍጻሜ ትንቢቱን ዶክተሩ ያላስተዋሉዋቸው ብዙ ነገሮች አሉ:: የመጀመሪያው ነጥብ እርሳቸው በሚስማማቸው መልኩ ለመተርጎም ሲሉ ሰዋስዋዊ ስህተት ሰርተዋል::« በአህዮች የሚቀመጡት » ሲል ብዙ አህዮችና ተቀማጮች ያሳያል:: «በግመሎች የሚቀመጡት» ሲል ደግሞ ብዙ ግመሎችና ተቀማጮች እንዳሉ ግልጽ ነው:: እንግዲህ እንደ እርሳቸው ትርጉም ከሆነ ብዙ አህዮች፣ብዙ ግመሎች፣ ብዙ ኢየሱሶችና ብዙ መሐመዶች በትንቢቱ ፍጻሜ ይሳተፋሉ ማለት ነው:: የትንቢቱ ፍጻሜ እንዲህ ነው:: ከኢሳይያስ 13-23 ያሉትን ምዕራፎች ያለው ክፍል እግዚአብሔር ወደፊት በአሥራ ሁለት አገሮች ሊያመጣ ስላለው ጥፋት የሚያስተምሩ ናቸው:: በጥፋቱ ባቢሎንና አረብ ይገኙበታል:: በምዕራፍ 21:1-12 ስለባቢሎን ውድቀት ሲናገር ከቁጥር 13-17 ስለ አረብ ውድቀት ይተነብያል:: ባቢሎን በምትወድቅበት ጊዜ ጠላቶችዋ ከምድረ በዳ መጥተው እንደሚጥ ሉአት ቃሉ ያስረዳል:: ከቁጥር 6-7 የጠላቶችን መምጣት የሚያስታውቅ ጉበኛ/ዘበኛ/እንደሚያቆሙ ጉበኛውም የጠላትን መምጣት በጥንቃቄ ተመልክቶ እንዲናገር እንዲህ ታዟል፦ «በከብት የሚቀመጡትን ሁለት ሁለት እየሆኑ የሚሄዱትን ፈረሰኞች፣በአህዮች የሚቀመጡትንና በግመሎች የሚቀመጡትንና ባየ ጊዜ በጽኑ ትጋት አስተውሎ ተግቶም ያድምጥ::» በዚህ ክፍል ባቢሎንን ለማጥፋት የሚመጡትን ሰዎች ሁለት ሁለት እየሆኑ በፈረሶች፣በአህዮችና በግመሎች ሆነው እንደሚመጡ ጠባቂውም መምጣታቸውን አይቶ እንዲያስታውቅ የተጻፈ ነው::[17] ወረድ ብሎም ከቁጥር9-10 ባቢሎን እንደወደቀች የእግዚአብሔር ቃል እስከነፍጻሜው ይገልጻል:: ከቁጥር 13-17 ደግሞ የአረብ ከብቶችና ሰዎች በተለይም የእስማኤል ዘር የሆነው የቄዳር ልጆች በሰይፍ እንደሚሞቱና የቄዳርም ክብር እንደሚጠፋ በግልጽ ተቀምጦአል::ይህ ደግሞ በዚያን ዘመን ተፈጽሞ አልፎ

አል። በአጠቃላይ ትንቢት በማመሳሰል ወይንም አንድ ቃል በመውሰድና ከሌላው ጋር በማገናኘት አይተረጎምም። ይልቁንስ ትንቢታዊ አውዱን መመልከትና ፍጻሜውን ከግምት ውስጥ ማስገባት አማራጭ የሌለው ተግባር ነው።

## ሸ/ ሥዕላዊ አገላለጦችን ቀጥተኛ ትርጉም አለመስጠት

ሌላው ትኩረት ሰጥተን የምንመለከተው ጉዳይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላሉት ሥዕላዊ አገላለጾችን ነው።እጅግ ብዙ ሥዕላዊ አገላለፆች በመጽሐፍ ቅዱሳችን ይገኛሉ። እነዚህም ሊታይ የማይችለውን መንፈሳዊ እውነት ሊታይ በሚችለው ቁሳዊ እውነት ገልጸው ያሳዩናል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎችም መንፈስ ቅዱስ እንደመራቸው በተለያየ መልኩ ተጠቅመዋቸዋል። ሥዕላዊ አገላለጾችን ቀጥተኛ ትርጉም ከሰጠናቸው ለማስተላለፍ የፈለጉትን መልዕክት መረዳት ያስቸግረናል። ከሥዕላዊ አገላለጽ ጀርባ ያለውን ትርጉም የማጥናት ሐላፊነትም አለብን። ለምሳሌ ዳዊት በመዝሙር እግዚአብሔር አለቴ ነው ሲል እግዚአብሔር መጠጊያው፣ መሸሸጊያውና ማረፊያው እንደሆነ ከአለት ጥንካሬ ጋር በማመሳሰል ዘምሮአል።በዚህ ክፍል ዳዊት እግዚአብሔር ድንጋይ ነው ማለቱ አይደለም።

በኢሳ.54:5 «ፈጣሪሽ ባልሽ ነው» ስለተባለ እንዴት እግዚአብሔር ሚስት ይኖረዋል? በማለት አንዳንዶች ይከራከራሉ። አምላካችን ሚስት አልነበረውም፣ የለውምም አይኖረውምም። «ፈጣሪሽ ባልሽ ነው » የተባለችው እውነተኛ ሴት ሳትሆን ጽዮን /እሥራኤል/ናት። በኢሳ.54:1-17 ያለው ክፍል የሚያስተምረው የጽዮን /እሥራኤል/ የወደፊት ክብር ነው። በመጀመሪያዎቹ ጥቅሶች እሥራኤል ከዚያ በፊት ማለትም በግብጽና በባቢሎን ምድር የደረሰባትን ውርደትና ስቃይ እያወሳ ያበረታታታል፣ ወደ ፊት ክብር እንዳላትም ይገልጻል። «ፈጣሪሽ ባልሽ ነው» ለምን ተባለ የሚል ጥያቄ ከተነሳ እግዚአብሔር ለእሥራኤል

የሚያደርግላት ጥንቃቄና እንክብካቤ በቁሳዊ መልኩ ማየት ስለሚያስቸግር አንድ ባል ለሚስቱ የሚያደርግላትን ጥንቃቄና እንክብካቤ በሥዕላዊ መልኩ በመጠቀም ነብዩ ኢሳይያስ የእሥራ ኤልና የእግዚአብሔር ግንኙነት ገልጾአል። በአጠቃላይ ጽዮን ሴት አይደለችም፣ እግዚአብሔርም ሚስት አያገባም። ነገር ግን የእግዚ አብሔርና የእሥራኤል ግንኙነት እንደ ባልና ሚስት ተደርጎ በሥዕ ላዊ መልክ ቀረበ እንጂ። እንዲሁም በሰፊው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ኢሳ.53 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስለኃጢአታችን ቤዛ ሆኖ መስቀል በትንቢት አሳይቶ በኢሳ.54 አንቺ ያልወለድሽ መካን ዘምሪ ጩኺ፣እልል በይ ይላል። በመሆኑም ፈጣሪሽ ባልሽ ነው የተባለው ቃል እስራኤልን ብቻ ሳይሆን ቤተክርስቲያንን ያጠ ቃልላል።

እንዲሁም በኢሳ.7:20 «በዚያን ቀን እግዚአብሔር ከወንዙ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ የራሱንና የእግሩን ጠጉር ይላጨዋል ምላጩም ጢሙን ደግሞ ይበላል።» ከሚለው አረፍተ ነገር እግዚአብሔር ሁሉም ነገር ያለው ሲሆን እንዴት ምላጭ ይከ ራያል? የሚል ጥያቄ ብዙ ጊዜ ይነሳል። በቅድሚያ ኢሳ.7:20 ያለው ሐሳብ በኢሳ.7:1-25 ካለው ክፍል ጋር የተያያዘ ነው። በክፍሉ እንደተገለጸው ነብዩ ኢሳይያስና ልጁም ያሱብ ወደ ይሁዳ ንጉሥ ወደ አካዝ ሄደው ከአሦርና ከእሥራኤል ነገሥታት በተላከበት ማስፈራሪያ እንዳይደነግጥና ከእግዚአብሔርም ምልክትን እንዲጠይቅ እንዲናገሩ እግዚአብሔር ልኳቸው ነበር።ነገር ግን አካዝ ምልክትን አልጠይቅም ብሎ አመጸ። ከዚህም የተነሳ ነብዩ ኢሳይያስ በአካዝና በሕዝቡ የሚደርሰውን መከራና ጉስቁልና ከቁጥር 17-25 ይዘረዝራል። በቁጥር 20 ይህም መከራ በይሁዳ ሕዝብ ላይ የሚመጣው «እግዚአብሔር ከወንዙ ማዶ በተከ ራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ» ነው ይላል። «መከራየት» እና «ምላጭ» የሚሉት ቃላት ሥዕላዊ አገላለጾች ናቸው። ምላጩ እውነተኛ ምላጭ ሳይሆን የአሦር ንጉሥ እንደሆነ «ከወንዙ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ» በማለት በግልጽ ያሳያል። መከ ራየት የሚለው ቃል ከሌላ ሰው ከፍሎ ማምጣት ሳይሆን በእግዚ አብሔር የተመረጠውን ሕዝብ ለመቅጣት አሕዛብን

/እግዚአብሔርን የማያመልክ ሕዝብ/ አስነስቶ ይጠቀማል ማለት ነው:: እንዲሁም «የራሱን ፣የእግሩንና የጢሙን ጸጉር፣ »ይላጨዋል የሚለው ሥዕላዊ አገላለጽ ሲሆን ክብርን ማሳጣትን፣ማዋረድን፣ ማጎሳቆልንና ለሽንፈት መዳረግን ለማሳየት ነው::[18] በዚያን ዘመን በእሥራኤልም ሆነ በመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ጸጉርና ጺም መላጨት የውርደትና የመሸነፍ ምልክት ነበር:: ኢዮ.1:20 ላይ ኢዮብ ንብረቱ ከጠፋና ልጆቹ ከሞቱ በኋላ ውድቀቱን ለማሳየት ራሱን ተላጨ:: በኢሳ.15:2፣ ኤር.47:5፤ 48:37፣ ሕዝ.7:18፣ አሞ.8:10፣ መክ.1:16 ተመሳሳይ ሐሳቦችን እናገኛለን:: «እግዚአብሔር ከወንዙ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ የራሱንና የእግሩን ጠጉር ይላጨዋል፣ ምላጩንም ጢሙን ደግሞ ይበላል» ማለት እግዚአብሔር ምላጭ ይከራያል ማለት ሳይሆን የአሦር ንጉሥን አስነስቶ የይሁዳ ንጉሥ አካዝንና ሕዝቡን ያዋርዳል ማለት ነው::

በመዝ.44:23 «አቤቱ ንቃ ለምንስ ትተኛለህ? ተነስ ለዘወትርም አትጣለን::» የሚለው ቃል በመዝ.121:4 «እነሆ እሥራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም::» ከሚለው ሐሳብ ጋር ይጋጫል የሚል ስሞታ አለ:: በእርግጥም እነዚህ ክፍሎች አውዳቸውን ተከትለን ካልተረጎምናቸውና የጥቅሶቹን የአፃፃፍ ዘዴ ካላወቅን የሚጋጩ ሊመስለን ይችላል::መዝ.44:23 ሥዕላዊ አገላለጽ ሲሆን መዝ.121:4 ግን አይደለም::መዝ.44:23 በሥዕላዊ አገላለጽ ስለተጻፈ በሰውኛ አገላለጽ ሰው ለማድረግ የፈለገውን ነገር የሚረሳው በእንቅልፍ ሲወድቅ ነው:: ስለዚህ መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ዝምታ እና የሕዝቡን ጩኸት ሰምቶ ለእርዳታ አለመፍጠኑን ለማሳየት በስዕላዊ አገለላጽ «አቤቱ ንቃ ለምንስ ትተኛለህ? በማለት ይጠይቃል:: በዚያው ጥቅስ ሁለተኛው ስንኝ ላይ ትርጉሙ እንዲህ ይላል« ተነስ ለዘወትር አትጣለን::» በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ይተኛል ወይንም ያንቀላፋል ማለት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ዝምታና ለእርዳታ አለመፍጠኑን ለማሳየት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉትን መንፈሳዊ እውነቶችን በብዙ ቦታ በሥዕላዊ

መንገድ ስለተገለጹ የአፃፃፉን ስልት ተከትለን ልንተረጉማቸው ያስጠ ፈልጋል::

## ቀ/ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከሌሎች ጋር አያይዞ ማጥናት

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የጠበቀ ቁርኝት ስላላቸው ዝምድናቸውን ባገናዘበ መልኩ መተርጎም አለባቸው:: አንዳንድ ሙስሊም ጸሐፊዎችና ሰባኪዎች አውዱን ሳያገናዝቡና የቋንቋን ሕግ እንኳ ሳይከተሉ እነርሱ ለማስተማር የፈለጉትን እንዲደ ግፍላቸው መጽሐፍ ቅዱስን በግድ ያናግሩታል:: ልብ ወለድ እንኳ አውዱን ተከትለን አይደል የምንተረጉመው? ሰማያዊ የሆነውን የእግዚ አብሔር ጥበብ ያለበትና የአምላክ መገለጥ የሆነውን ዘለዓለማዊ ቃል እኛ በወደድነው መንገድና ስርዓትን ባልተከተለ መልኩ ልንተረጉመው እንችላለን? መልሱን ለእናንተ እተወዋለሁ:: በቅርቡ «ፈጣሪ ማን ነው?» በሚል ርዕስ በተሰራጨው ካሴት ሰባኪው /አስተ ማሪው/ከቁርዓንና ከመጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሱ የአላህንና የእግዚአ ብሔርን ልዩነት ካስተማሩት ትምሕርት ማስተካከያ እንዲያደርጉ ለማሳሰብ እወዳለሁ:: በዚህ ስብከታቸው የመጽሐፍ ቅዱስን አውድ ሳይጠብቁ አንዳንዴ ቃላትን ፤በሌላም ጊዜ አንድን ሐረግ፣ ሲፈልጉም አንድን አረፍተ ነገር በመውሰድ መጽሐፍ ቅዱስ የማይለውን እንዲል በማስገደድ አስተምረዋል:: ቁርአንስ እንዲህ ይተረጉሙታል ወይ? ካልተረጎሙትስ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሊባል ያልታሰበውን ትርጉም ለምን ሰጡ? እንዲሁም ቁርአን የሚተረጎምበትስ መንገድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይ ነው ወይ ? መልሱ ለሰባኪው ሼክ ትቼ ወደ ዋናው ሐሳብ አልፋለሁኝ::

ሰባኪው ስለ መጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ሲያስተምሩ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፈጣሪ ማንነት በቂ መረጃ አይሰጥም በማለት ሲያስተምሩ በሁለተኛ ደረጃነት ያነሱት ሐሳብ መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች እግዚአብሔርን አዩ ስለሚል ትክክል አይደለም በማለት

ዲስኩር ሰጥተዋል። እኚህ ሼክ የፈጸሙት ስህተት ከአውድ ውጪ መተርጎማቸው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ለነብያቶቹ የተገለጠበት መንገድ አለመረዳታቸው ነው። ሰውዬውም ከሱራ 6:103 እና 7:143 በመጥቀስ አላህ ማንም ሊያየው እንደማይችል ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ በዘፍ.32:30፣ በዘጸ.24:9-11፣ በኢዮ.42:5፣ በኢሳ.6:1 እና በሌሎችም ሥፍራዎች ሰዎች ፈጣሪያቸውን እንዳዩ ስለሚናገር ቁርዓን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አምላክ ትክክለኛ ትምሕርት አይሰጥም ብለዋል። የእግዚአብሔር ቃል ሰዎች እግዚአብሔርን አዩ ሲል ምን ማለቱ ነው? ሁሉም ጥቅሶች አንድ ዓይነት ትርጉም አላቸው ወይ? ሰውስ እግዚአብሔር በሙሉ ክብሩ ተገልጦ በሥጋዊ ዓይኑ ማየት ይችላልን? እነዚህንና ሌሎችም ጥያቄዎች የመጽሐፍ ቅዱስን አውድ ባገናዘበ መልኩ መመርመር ነበረባቸው። ነገር ግን ይህንን አላደረጉም። እኛ ግን አውዱን ተከትለን ማጥናት ስላለብን ከዚህ ቀጥሎ ክፍሎቹን በየተራ እንመለከታቸዋለን።

በዘጸ.33:18-23 ሙሴ እግዚአብሔር በሙሉ ክብሩ ተገልጦ ለማየት ስለፈለገ ክብሩን እንዲያሳየው እንዲህ ሲል ጠይቆ ነበር «እርሱም ሙሴ:- እባክህን ክብርህን አሳየኝ አለ። እግዚ አብሔርም እኔ መልካምነቴን ሁሉ በፊትህ አሳልፋለሁ የእግዚ አብሔርንም ስም በፊትህ አውጃለሁ ይቅርም የምለውን ይቅር እላለሁ የምምረውንም እምራለሁ አለ።ደግሞም ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ።... ክብሬም ባለፈ ጊዜ በሰንጣቃው አለት አኖርሃለሁ ...ጀርባዬንም ታያለህ።ፊቴ ግን አታይም።» ሙሴ እግዚአብሔርን ማየት የፈለገው በራዕይ ወይንም በሕልም አልነበረም፣ ነገር ግን እግዚ አብሔር በክብሩ ተገልጦ ማየትን ነበር። ይህ በፍጹም የማይታሰብ ፤የማይሞከርም ተግባር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች አምላክን በሙሉ ክብሩ ተገልጦ በሥጋ ዓይናቸው አይተውታል አይለንም። እንዲያውም የእግዚአብሔር ክብር ባለፈ ጊዜ ሙሴ በሰንጣቃ ዓለት ውስጥ ነው የቆየው። ከፍ ብዬ በጠቀስኩት ክፍል « ጀርባዬን ታያለህ ፊቴን ግን አታይም» የሚለው ሥዕላዊ አገላለጽ ሲሆን ፊት የሚያሳየው የእግዚአብሔር ክብር ሲያልፍ

የሚል ጽንሰ ሐሳብ ሲኖረው ጀርባ የሚለው ደግሞ ክብሩ ካለፈ በኋላ በቦታው የተከሰተውን ክስተት ማየት ማለት ነው::[19] ለምሳሌ አንድ ጫካ ሲቃጠል ያላየ ሰው ከተቃጠለ በኋላ የመቃጠሉን ውጤቶች- አመድና ሌሎች ነገሮች ይመለከታል:: እንደዚሁም ሙሴ ያየው የእግዚአብሔርን ክብር ሳይሆን ክብሩ ካለፈ በኋላ ውጤቱን ነበር:: ሺኩም የተሳሳቱት በዚህ ነጥብ ላይ ነው:: ምክንያቱም ሰዎች አዩ የተባሉት ምን ዓይነት እይታ ነው? ብለው ለአንድ አፍታ እንኳን ራሳቸውን ስላልጠየቁ:: በዮሐ.1:18 «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው::»ይላል::

ይህን ስንል ግን ሰዎች የእግዚአብሔርን ክብር ማየት ስለ ማይችሉ በሌላ መንገድ ለነብያቶች አልተገለጠም ማለት አይደለም:: ቁርአን ስለ እግዚአብሔር መገለጥ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሰፋ ያለ ገለጻ ስለማይሰጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉትን መገለጦች እንመለከታለን:: እርሱ ለነብያቶችና ለቅዱሳን በተለያየ ጊዜና ቦታ በራዕይ፣በሕልም፣ በደመና ውስጥ ሆኖ በድምጽ፣ በእሳት፣ አምሳል እንዲሁም ለተወሰነ ጊዜ የሰውን ወይንም መልእክትን ቅርጽ በመያዝ ፣እና በተግባር ተገልጠ እናገኛለን:: በዘመን መጨረሻም በልጁ በክርስቶስ በኩል ተገልጧል:: እግዚአብሔር በእነዚህ መንገዶች መገለጥ የፈለገበት ምክንያት ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት እርሱ በሙሉ ክብሩ ተገልጦ ሊያየውም ሆነ በፊቱ ሊቆም የሚችል ሰው ስለሌለ ነው:: /1ጢሞ.1:17/:: በ1ኛጢሞ.6:16 እግዚአብሔርን ስለማየት እንዲህ ይላል:-«... ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም ለእርሱ ክብርና የዘላዓለም ኃይል ይሁን አሜን::» ሐዋርያው ጳውሎስ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ እንደጻፈውም ስጋዊና ደካማ በሆነው በሰው ዓይን በዚህ ታላቅ ብርሃን ውስጥ ያለውን ፈጣሪ በሙሉ ክብሩ ተገልጦ ማየትየማይሞከር ተግባር እንደሆነ ገልጸአል:: ለሙሴም የተነገረው ይህንኑ ነው:: ከሺኩ ጋር ፈጣሪን በሙሉ ክብሩ ማየት አይቻልም በሚለው የምንስማማ ይመስለኛል:: ነገር ግን አምላክ በሌላ መንገድ አልተገለጠም የሚሉት ሐሳብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስላልሆነ

ማስተካከል አለባቸው::

ይህ እንዳለ ሆኖ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ለተለያዩ ሰዎች በተለያየ መንገድ ተገልጧል::ይህንንም የተገለጠላቸው አምላክ እንዳዩት ተናግረዋል:: እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን አየነው ሲሉ በሙሉ ክብሩ ማለታቸው አይደለም:: በዘፀ.19:9-25 እግዚአብሔር ለሙሴና ለእሥራኤል ሕዝብ እንደተገለጠ ያትታል:: በቁጥር 9 እግዚአብሔር ለሙሴ በደመና እንደሚመጣ ነግሮት ነበር:: ከዚያም ከሦስት ቀን በኋላ በእሳት ተገልጦአል::እርሱ ለእሥራኤላውያን በሲና ተራራ ሲገለጥ ታላቅ ነጎድጓድና መብረቅ ከባድም ደመና እጅግም የበረታ ቀንደ መለከት ይሰማ ነበር:: ከዚህም የተነሳ ሕዝብ ሁሉ ተናወጠ:: ከዚያም እግዚአብሔር ለሙሴ በድምጽ ተናገረው::በዚህ ክፍል ፈጣሪያችን መገለጡን እንጂ ሙሴ ወይንም እሥራኤላውያን አምላክን ማየታቸው አይናገርም:: ሼኩ ግን በትምሕርታቸው ሙሴንና ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዳዩ አድርገው አቅርበውታል:: ትምህርታቸው ስህተት ነው::

ከዚህ ጋር በተያያዘ በዘጸ.24:9-11 ከእሥራኤላውያን የተመረጡ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳዩ እንዲህ ተጽፎአል:: «ሙሴም አሮንም፣ናዳብም፣አብዩድም ከእሥራኤል ሰባ ሽማግሌዎች ወጡ:: የእሥራኤልንም አምላክ አዩ ከእግሩም በታች እንደሰማይ መልክ የሚያበራ እንደ ብሩህ ሰንፔር ድንጋይ የሚመስል ወለል ነበር እጁንም በእሥራኤል አዛውንቶች ላይ አልዘረጋም እነርሱም እግዚአብሔርን አዩ በሉም ጠጡም::» በዚህ ክፍል እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን ያዩት በራዕይ ነው? በሕልም ነው? ወይስ በሙሉ ክብሩ ተገልጦ? በሰማያዊው ግርማው በብርሃን ውስጥ ሆኖ በሥጋዊ ዓይናቸው ሳይሆን እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን ያዩት በራዕይ ወይንም በመንፈሳዊ ዓይናቸው እንደሆነ እንመለከታለን:: ለዚህም ሁለት መረጃዎች አሉ:: እነዚህም ቁጥር 10 ላይ «...ከእግሩም በታች እንደሰማይ መልክ የሚያበራ እንደ ብሩህ ሰንፔር ድንጋይ የሚመስል ወለል ነበር::» የሚለው ዓረፍተ ነገር ነገሩ የተፈጸመው በራዕይ ውስጥ ሆነው እንዳዩ ያመላክታል:: ይህንንም ክፍል ከኢሳ.6:1-13፣ሕዝ.1:26እና ራዕይ1:10-16 እግዚ

አብሔር በራዕይ ከተገለጠባቸው መንገዶች ጋር ተመሳሳይ ነው። በቁጥር 10 የተገለጸው ሰንፔር የሚመስል ድንጋይ በትንቢተ ሕዝቅኤል1:26 እግዚአብሔር በራዕይ ሲገለጥ ከታየው ድንጋይ ጋር ተመሳሳይ ነው።እይታው በራዕይ ለመሆኑ ሁለተኛው መረጃ ቁጥር 11 ላይ «አዩ» የሚለው ቃል በእብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ በራዕይ ሆኖ መመልከት የሚል ትርጉም አለው። እግዚአብሔር በራዕይ ሆኖ መመልከትና የእግዚአብሔርን ክብር ማየት ፍጹም የማይገናኙና የተራራቁ ሐሳቦች ናቸው። ሰዎች የእግዚ አብሔርን ዙፋን በራዕይ ወይንም በመንፈሳዊ ዓይኖች ሲመለከቱ አምላካችን ምን ያህል ታላቅና ኃያል ጌታ እንደሆነ እንዲያስተውሉ እንጂ በራዕይ ያዩት ነገር እግዚአብሔር በሙሉ ክብሩ ተገልጦ ነው ማለት አይደለም።

በሌላ አንጻር ደግሞ በዘፍ.18:1 «በቀትርም ጊዜ እርሱ /አርብሃም/ በድንኳን ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት።» ይላል።ከዚህም ወረድ ብሎ አብርሃም ሦስት ሰዎችን እንዳየና ወደ ቤቱም እንደገቡ የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል። ከነዚህ ከሦስቱ ሰዎች ሁለቱ መላዕክቶች ሲሆኑ አንዱ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ስለዚህም መንፈስ የሆነው አምላክ ከሰዎች ጋር ለመነጋገር ለጊዜው ቁሳዊ በሆነ ነገር ይገለጣል።ይህም በነገረ- መለኮት ቋንቋ ( Antropomorhism) ይባላል።

መጽሐፍ ቅዱስ መላዕክቶች መናፍስት ናቸው ይላል ነገር ግን ለጥቂት ጊዜ በቁሳዊ አካል ይገለጣሉ። እግዚእብሔርስ እንዲህ እንዲገለጥ ማን ይከለክለዋል? እግዚአብሔር በወደደው መልኩ መገለጥ የአምላክ ሁሉን ቻይነት ጥያቄ ውስጥ ሊገባ አይችልም ካልን ደግሞ ይችላል። እግዚአብሔርን እኛ እንደምናስበው ብቻ እንዲህና እንዲያ መሆን አለበት ካልን አግባብ አይደለም።

በዘፍ.32:30 ያዕቆብ «... እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁት ሰውነቴም ድና ቀረች።» ሲል እግዚአብሔርን በሙሉ ክብሩ ተገልጦ በሥጋዊ ዓይኔ አየሁት ማለቱ ሳይሆን ለዘመናት ሰውንና ፈጣሪውን

ሲያታልል የነበረውን ያዕቆብ እግዚአብሔር ታሪኬን ቀየረው ማለቱ ነው:: ያኔ መልአኩ በሌሊት ተገልጦ ሲታገለው ካደረ በኋላ የጭኑን ሹሉዳ ነክቶት ስሙንም ቀየረ በረከትንም ሰጠው:: ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ወደ እርሱ ቀርቦ ሲባርከው፣ ስሙን ሲቀይርና ለእርሱ ያለውን ጥንቃቄ ለመግለጽ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁት አለ:: በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር በሥራው ተገልጦ አየሁት ማለት ነው:: ከዚያ በኋላ ያዕቆብ አታላይነቱ ቀርቶ የበረከት ሰው ሆኖአል:: ከዚህ በተመሳሳይ በኢዮ.42:5 «መስ ማትስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር አሁን ግን ዓይኔ አየችህ::» አለ:: ኢዮብ «ዓይኔ አየችህ::» ሲል የእግዚአብሔርን በሙሉ ክብር አየሁ ማለቱ አይደለም:: በኢዮ38:1እግዚአብሔር ለኢዮብ የተናገረው በአውሎ ነፋስ ውስጥ ሆኖ ነበር::

ኢዮብ አምላኩን አላየም ነገር ግን ድምጹን ሰምቷል:: በኢዮ.42:5 ኢዮብ ለመናገር የፈለገው አምላኩን የሚያውቀው ፈጣሪ እንደሆነ መሐሪ፣ ፍርድን የማያዳላ፣የሚባርክ፣ የሁሉ ገዢ፣ ሁሉን የሚያውቅ እና በአጠቃላይ በባሕሪው ነበር:: ነገር ግን አሁን በተግባር አይቼሃለሁ ነው የሚለው:: ኢዮብ በብዙ መከራና ስቃይ አልፎ ጻድቅ ፈራጁ እግዚአብሔር ወዴት ነው? እስኪል ድረስ መከራ ደርሶበት ነበር:: መጨረሻ ተስፋ ቆርጦ በነበረበት ጊዜ አምላኩ ወደርሱ ሲደርስና ሥራውን ሲያይ «መስማትስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር አሁን ግን ዓይኔ አየችህ» አለ:: የያዕቆብና የኢዮብ እይታ ከተግባር እንጂ ከእግዚአብሔር ሙሉ ክብር ጋር የተያያዘ አይደለም:: በዘጸ.33:11 «እግዚአብሔርም ሰው ከባልንጀ ራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር ሲል እግዚአብሔር በሙሉ ክብሩ ተገልጦ ያነጋግረው ነበር ማለት አይደለም:: በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔር በመገናኛው ድንኳን በደመና አምድ ተገልጦ በድምጽ ያናግረው ነበር:: ሙሴ ከአምላኩ ጋር ሸንጎ ቀጭ ብሎ እየተያዩ አይደለም ያናገረው:: ሙሴ የሚሰ ማው ድምጹን ብቻ ነው:: በአጠቃላይ ሙሴም ይሁን ሌሎች ሰዎች ፈጣሪ አምላክን በሙሉ ክብሩ ተገልጦ አይተውት አያውቁም፤ በሥጋዊ ዓይናቸው ወደፊትም አያዩትም:: ማንም የመ ጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ አንባቢ የሆንን መጽሐፍ ቅዱስን በአንድ

አቅጣጫ ብቻ እንዳናየው ነገር ግን አውዱን ተከትለው በቅንና እውነትን በሚናፍቅ ሕሊና እንድናጠናው እመክራለሁ።

## በ/ የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች ከብሉይ ኪዳን የጠቀሱአቸውን ክፍሎች እንዴት እንዳሰፈሩዋቸው ማወቅ

በአዲስ ከዳን ውስጥ ተጽፈው የሚገኙት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች እንዴት እንዳሰፈርዋቸው መረዳት አስፈላጊ ነው። አጻጻፋቸውን ካለመረዳት የተነሳ ብዙ ሰዎች ሲቸገሩ እመለከታለሁ። ከሁለት ዓመት በፊት አንድ ሙስሊም ጓደኛዬ መጽሐፍ ቅዱስ የመበላሸቱ ምልክት ከብሉይ ኪዳን የተጠቀሱ ሐሳቦች ቃል በቃል አለመሆናቸው ነው ብሎኛል። እንዲህ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ሌሎች ሰዎችም እንዳሉ አስባለሁ። በሐዋርያት ዘመን የነበረው የአፃፃፍ ዘዴ አሁን ካለው ጋር ልዩነት አለው። ስለዚህ በዚያን ጊዜ በነበረው የአፃፃፍ ስልት ተንተርሰን ነው መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል ነው ወይስ አይደለም ማለት የምንችለው። በሐዋርያት ዘመን የሥነጽሑፍ ሕግ መሠረት አንዳንዴ ቃል በቃል፤ በሌላ ጊዜም የጥቅሱን የተወሰኑ ቃላት ወይንም ሐረጎች በመውሰድ ይጠቅሱ ነበር።እንዲሁም የክፍሉን ሐሳብ ብቻ በመውሰድ መጻፍ የተለመደ ሲሆን ከሁለት ወይንም ከዚያ በላይ የብሉይ ኪዳን የነብያት መጽሐፍ የተወሰዱ ሐሳቦች አንድ ላይ አጣምረው ይጽፉ ነበር።

ከተለያዩ የነብያት መጽሐፍ የተወሰዱትን ሐሳቦች አንድ ላይ ሲጻፉ ከየትኛው መጽሐፍ የተወሰደ ተብሎ ይጻፋል? የሚል ጥያቄ መነሳት ያለበት ይመስለኛል።በዚያን ጊዜ በነበረው የሐዋርያት የሥነ-ፅሑፍ ሕግ ከአምስቱ ትላልቅ ነብያት /ኢሳይያስ፣ ኤርሚያስ፣ ሰቆቃወ ኤርሚያስ፣ ሕዝቅኤልና ዳንኤል/ እና ከአሥራ ሁለቱ ትናንሽ ነቢያት ተወስዶ እንደሆነ በትላልቅ ነብያት ስም ይጻፋል።ይህ ሕግ በዚያን ዘመን የሚሠራ ነበር፤ ነገር ግን በእኛ ዘመን ስለማይሰራ ስህተት ነው ማለት አንችልም።ይልቁንስ ይህን ሕግ ተረድተን በዚህ መሠረት መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎም

አለብን:: እንደዚህ ዓይነት ብዙ ጥቅሶች ያሉ ሲሆን አንድ ክፍል እንመልከት:: በማር.1:2-3 ያለው ሐሳብ የተወሰደው ከኢሳ.40:3 እና ከሚል.3:1 ነው:: ነገር ግን «በነብዩ በኢሳይያስ እንደተጻፈ» ተብሎ ነው የተገለጸው::ኢሳይያስ ከትላልቅ ነብያት አንዱ ሲሆን ሚልክያስ ደግሞ ከትናንሽ ነብያት ውስጥ ነው:: ቅዱስ ማርቆስ ከሁለቱ የትንቢት መጽሐፍት ወስዶ በአንድነት ሲጽፍ የትልቁን ነብይ /ኢሳይያስን/ ስም ተጠቅሞአል:: የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች መንፈስ ቅዱስ እንደመራቸው በራሳቸው ዘመን ታሪካዊ አውድ ስለጻፉ ይህንን ተረድተን መተርጎም ይኖርብናል:: ትርጉማችንም መጽሐፍ ቅዱስን ወደ እኛ አመለካከት አምጥተን ሳይሆን እኛ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ሄደን መሆን አለበት::

## ተ/ የመጽሐፉ ክፍል ስለምን እንደሚያስተምር መገንዘብ

መጽሐፍ ቅዱስ ጥልቅ የሆኑ መንፈሳዊና ከዕለት ተዕለት ኑሮአችን ጋር የተቆራኙ እውነቶችን የያዘ ስለሆነ ከቃላቶቹ ጀርባ እግዚአብሔር አምላክ ለማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት መረዳት በጣም ጠቃሚ ነው:: ላይ ላዩን ብቻ እያየን በግምት ለመተርጎም ከተነሳን ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ ዓይነት ይሆናል:: የእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን አጠቃላይ ሐሳብ ጠብቀን ከሌሎች ክፍሎች ጋር በማገናዘብ መተርጎም አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል እንዳልሆነ በካሴት ከተሰራጩት ጥቅሶች ሁለቱን ብንመለከት ደስ ይለኛል::ወደ ጥቅሶቹ ከማለፋችን በፊት አንድ ነገር ማለት እፈልጋለሁ:: መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ስለሆነ እውነተኛነቱን ከራሱ ማረጋገጫ መስጠት እንዳለብን አምናለሁ መጽሐፍ ቅዱስን ማንም እንዳይነካው ብለን መናገር የለብንም:: በተለያየ ጊዜ ለሚነሱ ትክክለኛ ሳልሆኑ ተቃውሞዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት ከጥንቱ ቤተክርስቲያን ጀምሮ የተለመደ ተግባር ነው:: ማንኛውም ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ተነክቷል ብሎ ጦር መስበቅ የለበትም:: በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል ሆኖ ሳለ ማንም በፈለገው መንገድ ማንቋሸሹ አግባብ አይደለም:: ነገር ግን እውነተኛውን የእግዚአብሔር ፈቃድ በፍቅር እየገለጽን እንድናስተምር

ከጌታ የተሰጠን አደራ ነው:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል የሚጠሏችሁን ውደዱ፣ የሚረግሙአችሁን መርቁ፣ ለሚያሳድዱአችሁ ጸልዩ ይላልና:: ይልቁንም ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ምሕረት እንዲ በዛላቸውና ወደ ጌታችንና መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ እንዲመጡ ልንጸልይላቸው ይገባል::

ወደ መጀመሪያው ሐሳብ ልመልሳችሁና ጥቅሶቹ የሚገኙት በዮሐ.1:1 እና በዘፍ.1:1 ላይ ነው:: በዮሐ.1:1«በመጀመሪያው ቃል ነበረ...» ሲል በዘፍ.1:1«በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ::» ይላል:: ሙስሊሞችንም ሆኑ ሌሎች ጥቅሶቹን በደንብ ያልተረዱ ሰዎች ቀዳሚ መሆን ያለበት ዘፍ.1:1 ወይስ ዮሐ.1:1? አሊያም ሁለቱም የሚያስተምሩት ስለ አንድ ጊዜ ነው? ከሆነስ እንዴት? የሚሉ ጥያቄዎች ያነሳሉ:: ለእነዚህ ጥያቄዎችም ትክክለኛ ያልሆኑ ግምታዊ መልሶችን ይሰጣሉ:: ክፍሎቹን በደንብ ሳናጠና ግምታዊ ድምዳሜ መስጠት እጅግ ትልቅ ስህተት ነው::በእነዚህ ክፍሎች ያለው ሐሳብ እንዲህ ነው:- በዮሐ.1:1 እና በዘፍ.1:1 ላይ «በመጀመሪያ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድ ዓይነት ጊዜን /ሰዓትን/ነው::[20] በሁለቱ ጥቅሶች የግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስም የተጠቀመው ቃል "enarche" የሚል ሲሆን የሚያመለክተውም እግዚአብሔር በሰማይና በምድር ያሉትን ነገሮች መፍጠር ሲጀምር የጀመረበት ጊዜ ወይንም ጅማሬውን ያሳያል:: በዚህ አጋጣሚ መረዳት ያለብን «ጊዜ» ራሱ የተፈጠረ ሲሆን ከሰ ማይና ምድር አፈጣጠር ጋር የተያያዘ ነው::መጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ የፍጥረት አካል እንደሆነ ያስተምራል:: በቅርቡ ይፋ በሆነውም የሳይንስ ግኝት መሠረት «የጊዜ አፈጣጠር ከሰማይና ከምድር አፈጣጠር ጋር» የተቆራኘ መሆኑን ያስረዳል:: እግዚአብሔር ፍጥረትን ከመፍጠሩ በፊት «ጊዜ» አልተፈጠረም:: በዘፍ.1:1 «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ::» ሲል ከሁሉም ነገር በፊት በቀዳሚነት የሆነው ነገር የሰማይንና የምድር መፈጠር ነው ማለቱ ሲሆን ጊዜም የጀመረው በዚያ ነጥብ ላይ ነው::የሰው ልጆች ታሪክና ሌሎችም ክስተቶች የመጡት ከዚያ በኋላ ነው::ዮሐ.1:1-3 ደግመን እንመልከት« በመጀመሪያው ቃል ነበረ: - ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ::

ይህም በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።» በዚህ ክፍል «መጀመሪያው» የሚለው ቃል በዘፍ.1:1 እንደተመለከትነው የፍጥረት ጅማሬ ወይም እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን መፍጠር ሲጀምር ማለት ሲሆን ከዚያ ጊዜ በፊት ቃል እንደነበረ እንረዳለን። ይህንንም ቃል በፍጥረት ጅማሬ ላይ ከእግዚአብሔር /ከአብ/ ጋር ነበር። ፈጣሪ ከመሆኑ የተነሳና ከፍጥረት ሁሉ በፊት ስለነበረ /ዘላለ ማዊ /ስለሆነ ሰማይንና ምድርን ሲፈጠሩ የፈጠረው እርሱ ነው።ቃልም/ ኢየሱስ ክርስቶስ/የፍጥረት ጅማሬ ከመጀመሩ በፊት እርሱ ነበረ። ይህንን እውነት ለማሳየት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ.8:58 «እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው።» በዚህ ሥፍራ «አለሁ" የሚለው ቃል ዘለዓለማ ዊነቱን የሚገልጥ ሲሆን« ነበርሁ» ቢል ኖሮ ጅማሬ እንደነበረው ይገልጽ ነበር። በራዕ.1:18 «... ከዘላለም እስከ ዘላለም ሕያው ነኝ።» በማለት ከፍጥረትና ከጊዜ ጅማሬ በፊት እንደነበረ ፤አሁንም እንዳለና እንደሚኖር ተናግሮአል። በአጠቃላይ በዘፍ.1:1 እና በዮሐ.1:1 «መጀመሪያ» የሚለው ቃል የፍጥረትንና የጊዜን ጅማሬ የሚያሳይ ሲሆን ቃልም /ኢየሱስ ክርስቶስም/ በዚያ ጊዜና ከዚያም በፊት እንደነበረ፣ዘላለማዊና የነገሮች ፈጣሪ እንደሆነ ለማሳየት ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ በዘፍ.1:26« እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር፤ የባህር ዓሣዎችንና የሰማይ ወፎችን፡-እንስሳትንና ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።» ስለሚል እግዚአብሔር መልክ አለው ወይ? የሚል ጥያቄ ከብዙዎች ይነሳል። ይህንን ክፍል በጽሑፌ ለመዳሰስ ያሰብኩት አንድ ሙስሊም መምሕር ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ተርጉመውት/ ተረድተውት/ ባሰራጩት ካሴት ስለሰማሁ ነው።መቼም ሰው ሁሉ እውነቱን እስኪያውቅ ድረስ ሊሳሳት ስለሚችል መምሕሩን ከመኮነን ይልቅ ትክክለኛው መልዕክት ምን እንደሆነ ለርሳቸውም ሆነ ለሌሎች ለመግለጽ እፈልጋለሁ። በዚህ የመ ጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አውዱን ስንመለከት እንዲሁም በአጠቃላይ የመ ጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስናጠና «በመልካችን እንደ ምሳሌያችን»ማለት ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ እንረዳለን።እግዚአብሔር አምላክ

«በመልካችን እንደምሳሌያችን» ሲል እኛ እንደምናስበው ቁሳዊ አካል ማለት አይደለም:: እግዚአብሔር በራሱ ውጫዊ መልክና ቁመና የለውም፤ እግዚአብሔር መንፈስ ነውና:: በዚህ ሥፍራ እግዚአብሔር ለማለት የፈለገው ቁሳዊ አካልን ሳይሆን ሰው ከሌሎች እንስሳት በተለየ ሁኔታ ውስን በሆነ መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር የባህሪይ ተመሳሳይነት እንዳለው ለማመልከት ነው:: እግዚአብሔር በባሕሪው ፍጹም ነው::ይህም ማለት እርሱ ሁሉን ያውቃል፤ሁሉን ይገዛል፣ጻድቅና ቅዱስ ነው፤ለጥበቡ መጨረሻ የለውም፤ሁሉን ቻይ ነው፤በሁሉ ሥፍራ ይገኛል::ለፍጥረቱም ፍጹም ፍቅር አለው ከሰው ጋር ሕብረት ያደርጋል፣ያስባል፣ ይናገራል፣ በሰዎች ክፋት ያዝናል እንዲሁም ሌሎችም ባሕሪያት አሉት:: ሰውንም ስንወስድ ውስን የሆነ እውቀት ጥበብ፣ ኃይል፣ ፍጥረታትን የመግዛት ብቃት፣ ፍቅርን ማሳየት፣ከሰውና ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ማድረግ፣ማሰብ፣ ማቀድ፣መናገር፣ ማዘንና መደሰት፣እና ሌሎችም ባሕሪያት እግዚ አብሔር ሰውን ሲፈጥር በሰው ውስጥ አኑሮአል::ከሌሎች እንስሳት በተለየ መንገድ ሰውን «በመልኩ ፈጠረ» ሲል ውሱን በሆነ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር በባሕርይ ይመስላል ማለት ነው:: ይህም የሆነበት ምክንያት እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር እፍ ካለበት የሕ ይወት እስትንፋስ የተነሳ ነው:: ይህ ማለት ግን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በቁሳዊ አካል ይመስላል ወይንም በባህሪይ ፍጹም አንድ ነው ማለት አይደለም:: «ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር:: »ካለ በኋላ ምድርና በውስጡ ያለውን ሁሉ እንዲገዙ ስልጣን ሰጥቷቸዋል:: እግዚአብሔር በባሕሪው ገዢ ነው:: ስለዚህ ይህንን የምድሩን የገዢነትን ስልጣን ለሰው አሳልፎ የሰጠው ለገዢነት የሚያበቃውን ባሕሪይ በውስጡ ስላስቀመጠ ነው:: አውዱ የሚያሳየን ሰው በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠረ ሲባል ቁሳዊ የሆነው ነገር ሳይሆን የባህርይ ተካፋይነትን ለማመልከት ነው::

ሙስሊሞች በሉቃስ 12:51-53 ባለው ስፍራ ኢየሱስ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም ይልቁንስ አባትን ከልጅ እናትን ከልጅዋ ልለያይ መጣሁ እንጂ ሲል በኢሳ.9:6 የሰላም አለቃ ተብሎ ተጠ ቅሶአል::ይህ ግልጽ ግጭት አይደለምን? ሲሉ ይጠይቃሉ::

የክርስቶስ ወደዚህ ምድር መምጣት ዓላማ ቤተሰብን ለማፍረስ ሳይሆን ሰውንና እግዚአብሔርን ለማስታረቅ ነው:: ይህም በመስቀል ላይ በመሞት የሰዎችን ኃጢአት ተሸክሞ ከአብ ጋር ለማስታረቅ ነው:: የሰው ዘር ሁሉ በኃጢአት ምክንያት መሞት ነበረበት:: ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ፈንታ ሞቶ ከአብ ጋር አስታረቀን:: በሰውና በእግዚአብሔር መካከልም ሰላምን አደረገ:: ነገር ግን እርሱ የመጣው ኃጢአት ወደነገሰበት፣ የጨለማው ገዢ /ሰይጣን/ ወደሚገዛበት ምድር ስለሆነ ክርስቶስና በእርሱ ያመኑት ተቀባይነት አያገኙም:: የሰላም አለቃና የዓለም ብርሃን የሆነው ጌታ ኢየሱስ ሲገለጥ በዓለም ላይ ያለው የጨለማው ገዠ በእርሱና በሕዝቡ ላይ ይነሳል:: ከዚህም የተነሳ ነው ቤተሰብ የሚከፋፈለው፣ ቤተሰብ ውስጥ ሰዎች ጌታ ኢየሱስን ሲያምኑ ሰላምን የሚያደፈርሰው አዲሱ አማኝ ሳይሆን የጨለማው ገዥ/ሰይጣን/ ነው:: ክርስቶስን ያመኑ ሰዎች ያላመኑትን አያሳድዱም ወይንም ሰላምን አያደፈርሱም:: ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም የሚለው ካላመኑት ወገኖች ስደትና ጦርነት የሚመጣ መሆኑን ለማመልከት ነው:: ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ እንዲዋጉ ወይንም እንዲጣሉ አላስተማረም:: ይልቁንስ ግራ ጉንጭህን ለሚመታህ ቀኝህን አዙርለት ብሏል:: እርሱ የሰላም አለቃ ስለሆነ እርሱ የሚሰጠው ሰላም አለም እንደሚሰጠው እንዳልሆነና ሰላሙንም እንደሚተውላቸው ለሐዋርያቱ የተናገረውን በዮሐ.14:27 ተጽፎአል:: ስለዚህ በሉቃ.12:51-53 ሰዎች ክርስቶስን ሲያምኑ ከሌሎች ስደት፣ ግርፋት፣ ነቀፋ፣ስድብና መገለል እንደሚደርስባቸው የሚመለከት ነው::ከዚህም የተነሳ ያመኑት ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው የመሰደድ አጋጣሚ እንደሚኖር ያስተምረናል:: የሰላሙ መጥፋት ምክንያት ኢየሱስ ሳይሆን ሰይጣን ነው:: ከዚህ የተነሳ ከፍ ብለኝ ያየናቸው ክፍሎችም አይጋጩም::

በዘዳ.23:1-6 ያለው ክፍል አንዳንድ ሙስሊም አስተማሪዎች ከእግዚአብሔር ፍርድ ሙስሊም አስተማሪዎች ጋር ይጋጫል ይላሉ:: በዚህ ክፍል በቁጥር 1 ቁላው የተቀጠቀጠ

ብልቱም የተቆረጠ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ ይላል:: በቁጥር 2 ደግሞ ዲቃላ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ እስከ አስር ትውልድ ድረስ ይላል። ከቁጥር 3-6 ደግሞ ሞአብአዊያንና አሞናዊያን እስከ አስር ትውልድ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግቡ ይላል:: ስለዚህ እግዚአብሔር ማዳላቱ አይደለምን? በማለት የእግዚአብሔርን ጻድቅነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባሉ::

በዘዳግም 23:1-8 ያለው ክፍል ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ መግባት ስለሌለባቸው ሰዎች ይዘረዝራል:: እንዳይገቡ የተከለ ከሉበት ምክንያት አሉዋቸው:: በቁጥር 1 ቁላው የተቀጠቀጠ ብልቱም የተቆረጠ ሰው ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ የተባለበት ምክንያት በመካከለኛው ምስራቅ ወንድ ሕፃናት ጃንደረባ እንዲሆኑ ብልታቸውን መቁረጥ ወይንም መቀጥቀጥ የተለመደ ሥራ ነበር:: እነዚህ ወንዶች በአህዛብ ቤተመቅደሶች ለአምላካቸው አገልጋዮች እንዲሆኑ ይደረጋሉ:: እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ እንዳይገቡ የተከለከሉት የአህዛብን የአምልኮ ስርዓት ወደ እግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንዳያስገቡ ነው:: ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር የሰዎችን የዘር አካል የፈጠረው ለመራባት ስለሆነና በዚህ ክፍል ያለው ሁኔታ ከእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ፈቃድ ጋር ስለሚቃረን ነበር:: ይህም ቢሆን በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ኃጢአት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የኃጢአትን ዕዳ ስለከፈለ በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ባመኑት ላይ ልዩነት አይደረግም:: በሌላ በኩል ደግሞ በቁጥር 2 ዲቃላ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ እስከ አስር ትውልድ የተባለበት ምክንያት ለእግዚአ ብሔር ጉባኤ ተገቢ ባለመሆኑ ነው:: ዲቃላ ማለት 2 ዓይነት ትርጉም ሊኖረው ይችላል:: አንደኛው ከጋብቻ ውጪ የተወለደ ማለት ነው:: እግዚአብሔር ጋብቻን መስርቷል:: ከዚያ ውጭ የሚወለድ ሁሉ በዝሙት ምክንያት ነው:: ስለዚህ ከእግዚአብሔር እቅድና ፈቃድ ጋር ስለሚጣረስ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚወለዱ እስከ አስረኛ ትውልድ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ እንዳይገቡ እግዚአብሔር ደንግጓል:: ያም ቢሆን ዛሬ በክርስቶስ በማመን ሰው ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲገባ እግዚአብሔር

በፍቅሩና በጸጋው ሁሉን ስለፈጸመ በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ እንዲድኑ ተወስኖአል:: ሁለተኛው ትርጉም ሊሆን የሚችለው በዘካ.9:6 እንደተገለጠው የተደባለቀ ወገን ማለት ነው:: (Mixed Race) እነዚህ ሕዝቦች ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ እንዳ ይገቡ የተባለበት ምክንያት የጣኦት አምልኮ ስርዓት ወደ እግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንዳያስገቡ ነው::

ከቁጥር 3-6 ሞአባዊያንና አሞናዊያን ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግቡ የተባሉበት ምክንያት እስራኤላውያን ከግብጽ ሲመለሱ ከመቀበል ይልቅ ጠላት ስለሆኑባቸው ስለሠሩት ስለዚያ ኃጢያት ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ እስከ አስር ትውልድ ድረስ እንዳይገቡ እግዚአብሔር ወስኖባቸዋል:: በእነዚህ ጥቅሶች ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ እንዳይገቡ የተከለከሉ ሰዎች በብሉይ ኪዳን ስርዓት ወደ ቤተመቅደስ ለመግባት ብቁ ባለመሆናቸው እንጂ እግዚአብሔር ፍርደ ገምድል ሆኖ አይደለም:: እግዚአብሔር ጻድቅ ነው:: የሰውም ፊት አይቶ አያዳላም:: ኃጢአተኛው ይቀጣል ጻደቁንም ያከብራል:: ቅጣቱ እስከ አስር ትውልድ ምሕረቱም እስከ ሺህ ትውልድ ነው:: እግዚአብሔርን ተሳስተሃል ሊለው የሚችል ማነው? የእግዚአብሔርንስ ፍርድ ማን ሊያሻሽለው ወይንም ሊመረምረው ይችላል?

አንዳንድ ሙስሊሞች በመሳ.15-16 ያለው የሳምሶን ታሪክና በ1ኛ ሳሙ.15:1-16 ስለ አማሌቅ መጥፋት የሚተርኩ ክፍሎች ከእግዚአብሔር ምሕረትና ጽድቅ ጋር ይቃረናሉ በማለት ይከሳሉ::

በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ጻድቅ እንደሆነና ኃጢአተኛን እንደሚቀጣ እንዲሁም ጻድቁን እንደሚያከብር ማወቅ አለብን:: በሌላ አንፃር ደግሞ እርሱ መሃሪ ነው:: በንስሐ ለሚመለሱት ይቅርታን ያደርጋል:: በትንቢተ ዮናስ ከኃጢአታቸው ብዛት የተነሳ ሊጠፉ የነበሩ የነነዌ ሰዎች ንስሐ በመግባታቸው ምሕረት

አግኝተዋል:: በመሳ.15-16 ባለው ክፍል እግዚአብሔር በሳምሶን በኩል የሰራው ሥራ የእርሱን ትክክለኛ ፍርድ የሚያሳይ እንጂ የእግዚአብሔር ባሕርይ የሚቃረን አይደለም:: በሳምሶን ምክንያት ንብረታቸው የተቃጠለባቸውም ሆነ የሞቱት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በደልን የሚያደርሱና እግዚአብሔርን የማያመልኩ አመፀኞች ነበሩ:: በአመፃቸውም ምክንያት እግዚአብሔር ቀጥቷቸዋል:: ሳምሶንም ራሱ ማድረግ የማይገባውን ባደረገ ጊዜ ስለሰራው ኃጢአት መከራና ስቃይ ደረሰበት:: ታሪኩንም በሞት ተዘጋ:: ልብ ልንል የሚገባን እግዚአብሔር ሳምሶንም ሳይቀር ኃጢአተኞችን ቀጥቷል::መሳ.16:2 ይህም ፈጣሪ አምላክ በሐጢአት ላይ ያለውን ጠንካራ አቋም የሚያሳይ እንጂ ጽድቁን አይጣረስም:: በ1ኛ. ሳሙ.15:1-6 ያለውም ሐሳብ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው:: ኃጢአታቸው ስለበዛ እና እስራኤላውያን ከግብጽ ምድር በወጡ ጊዜ ከመቀበል ይልቅ ጠላት ስለሆኑባቸው ስለሰሩት ኃጢአት እግዚአብሔር ከሕፃን እስከ አዋቂ እንዲጠፉ አዞአል:: እግዚአብሔር በፍርዱ አይሳሳትም ማንም ሊጠይቀውም አይችልም:: እኛ እግዚአብሔርን እንዲህና እንዲያ አድርግ እንለው ዘንድ ማን ነን? እንዲህ ዓይነት ጥያቄ የሚያነሱ ሰዎችም አመለካከታቸውን ሊያስተካክሉ ይገባቸዋል:: የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ፍርደ ገምድል ከሆነ ነብዩ መሐመድ በፈጣሪ ስም የሰሩት በደል ምን እንበለው?እስልምናን ያልተቀበሉ ሰዎች እንዲገደሉ ሲያዙ በስሙ ይህን ሁሉ የተሰራው አምላክስ ጻድቅ ወይስ ፍርደገምድል? ነብዩ መሐመድስ በመዲና የነበሩት ሶስቱ የአይሁድ ጎሳዎች /ባኑ ቃኑቃህ፣ባኑ አል ነዲር እና ባኑ ቁረይዛ ለዓመታት ከነበሩት ከተማቸው ሲያባርሩ ሲገሉና ሲዘርፉ እንደነበሩ የታሪክ መጽሐፍት ያስረዱናል:: ከመዲና በስተሰሜን በኬይባይ ይኖሩ የነበሩትን አይሁዶች ወንዶቻቸውን ገድለው ሴቶችና ልጆቻቸው ባሪያ ሲያደርጉ የአይሁዶቹ ኃጢአት ምን ነበረ? በአላህ ስም ነብዩ መሐመድ ይህን ሲያደርጉ አላህ የፍትህ አምላክ ነው ብለው አይደለምን?